የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
Jobs Creation Commission
Federal Democratic Republic of Ethiopia

ቁጥር ሥ/ዕ/ፈ/ኮ/5487/2013

ቀን 4/13/2013ዓ.ም

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር

ለገጠር የሥራ እድል ፈጠራ ቢሮ

**ድሬደዋ**

ጉዳዩ፡- ሁለተኛ ዙር ብሩህ የንግድ ፈጠራ ኃሳብ ውድድርን ለወጣቶች ይፋ ማድረግን ይመለከታል፡፡

የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን ውጤታማ የሆኑ ለብዙዎች የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ አንተርፕሪነሮችን ወደ ኢንተርፕይዝ ደረጃ ሊያሸጋግር የሚችል ዘላቂ የሆነ መንገድ መፍጠር አላማው አድርጎ እየሰራ ይገኛል። ለዚህ ሥራ አዳዲስ ፈጠራንና የፋይናንስ አማራጮችን ያካተተ የኢንቨስትመንት አደጋዎችን/ክፍተቶችን በመሙላት አንተርፕሪነሮችን እና ከፍተኛ ዕድገት ያላቸው ንግዶችን መደገፍ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

በመሆኑም ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በጋራ በመሆን ደረጃውን የጠበቀ ሁለተኛውን ዙር የብሩህ ንግድ ፋጠራ ኃሳቦች ውድድር በማዘጋጀት የሀገራችንን ቁልፍ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶች አሰልጥኖና አወዳድሮ ለአሸናፊ አንተርፕሪነሮች መነሻ ገንዘብ በመስጠትና በማብቃት ሥራ ፈጣሪ ድርጅቶችን እንዲያቋቁሙ ይሰራል፡፡ ይህ ውድድር በቴሌቪዥና በሌሎች ማህበራዊ ድህረ-ገፆች የሚተላለፍ ሲሆን ሌሎች ወጣቶችም እንዲነሳሱ አስተማሪ ፕሮግራሞችን ይቀርባሉ፡፡

ስለሆነም ሁለተኛው ዙር የብሩህ የንግድ ፈጠራ ኃሳብ ውድድር **ከመስከረም 5፣ 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምተት 5፣2014 ዓ.ም** ለአመልካቾች ክፍት ይሆናል። በዚሁ መሰረት በክልላችሁ የሚገኙ  አዳዲስ የንግድ ፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶች በዚህ ውድድር መሳተፍ እንዲችሉ  ለዚህ ውድድር ተብሎ በተዘጋጀው ድህረ-ገፅ **www.bruh-et.com** ወይም የኢንተርኔት ችግር ለሚገጥማቸው ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክነው የማመልከቻ ቅፅ ከቢሯችሁ በመውሰድ ሞልተው **በፖስታ ሳጥን ቁጥር 25534 አዲስ አበባ**  በመላክ እንዲመዘግቡ አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉላቸው እንጠይቃለን። በተጨማሪም ይህን ውድድር ለእጩ ተወዳዳሪ ወጣቶች ለማስተዋወቅ ይቻል  ዘንድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክነውን ፖስተር በማስታወቂያ ቦርድ ላይ በመለጠፍ  እና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለወጣቶች መረጃው እንዲደርስ የተለመደ ትብብራችሁን  በማክበር እንጠይቃለን።

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ወ/ሪት ቅድስት ከፈለኝ ስልክ ቁጥር +251973078111 ወይም አቶ ሮቤል ሳምሶን ስልክ ቁጥር +251911106490 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አለምፀሀይ ደርሶልኝ ለገሰ
Alemtsehay Dersolign Legese
አዳዲስ የስራ ዕድል ፈጠራ ፕሮጀክቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
Director Innovative Jobs Creation & Project Directorate